# <u>የአባ ቀውስጦስ ቀጣይ የማፈራረስ ዘመቻ በአትላንታ፤</u>

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር በጎ ፈቃድና ከቤተ ክርስቲያን ሕግ ውጭ ቋንቋን፣ ዘርንና ጎሳን ምክንያት አድርጎ ያለ አንዳች ፈሪሃ እግዚአብሔር በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ እንዲሾም በመደረጉ ቤተ ክርስቲያኗ በታሪኳ አጋጥሟት ወደ ማያውቅ ምስቅልቅል ውስጥ የገባች መሆኗ ለማናችንም ግልጽ ነው። በዚህም ምክንያት ሕገ ቤተ ክርስቲያን መከበር አለበት ያሉ ምዕመናንና ጳጳሳት በስደት ላይ ሆነው በራሳቸው ሲኖዶስ የሚመሩ ሲሆን፣ በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ይህ ዓይነቱን መፈንቅለ-መንበር የሚቃወሙና ሕገ-ወጡን ፓትርያርክ የማይቀበሉ ኢትዮጵያውያን ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ነው።

በአንጻሩ ደግሞ በዘመናችን በኢትዮጵያውያን አእምሮ የተቀረጸው ክፉ የዘር በሽታ በመላው የኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት ያለውን ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ሕግ እንዳያስተውሉና እውነቱን እንዳይቀበሉ የጋረዳቸው ኢትዮጵያውያን አልታጡም። በእንደዚህ ዓይነት ስሜት "ገለልተኛ" ነን የሚሉ በተለይም በሰሜን አሜሪካ ያሉ እነዚህ ክፍሎች የሚከተሉት መስመር በየትኛውም የክርስትና ዓለም ተቀማይነት የሌለው አካሄድ እንደሆነ ይታወቃል። በሊቀ ጳጳስ የማይመራ ቤተ ክርስቲያን ራስ የሌለው አካል ማለት ነውና። እነሱም ሕሊናቸው ይህን ይመሰክራል። በዚህም ምክንያት አንዳንዶቹ በመጀመሪያ ይከተሉት የነበረውን መስመር በመልቀቅ የአባ ጳውሎስን ትዕዛዝ ከሚያስፈጽሙ ጳጳሳት መካከል ለእነርሱ የሚመቻቸውን በሕገ ወጥ መንገድ ለማግኘት መፈለጋቸው አልቀረም። ይህ ደግሞ ይዘውት ከተነሱት ዓላማ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ የራሳቸውን ምዕመናን በማስቀየምና በአጠቃላይ መሐል ላይ ቆመው በአባቶች መካከል ለሚታሰበው እርቅና ለቤተ ክርስቲያኒቱ ውሕደት የመሰናክል ድንጋይ ሆነው ይሰተዋላሉ።

በይበልጥም ደግሞ "የገቢያ ግር ግር ለሌባ ያመቻል" እንዲሉ በዘመናችን የተከሰተውን ይህንን መጥፎ አጋጣሚ ተጠቅመው ራሳቸውን ለሹመት ያዘጋጁ ሆድ አደር ጳጳሳትና ካህናት በአፈሙዝ ታጅቦ በተቀደሰው መንበር ላይ ለተቀመጠው ባለሥልጣን ሰጥ ለጥ ብለው መታዘዛቸው ሳያንስ በክህነታዊ ሥራቸው ላይ ተደራቢ የፖለቲካ ተልዕኮ አንግበው በሰላም ውሎ የሚገባውን በሰሜን አሜሪካ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ እርስ በራሱ ሲያባሉት ይስተዋላሉ። በዚህ መንገድ አባ ጳውሎስን ካልተቀበላችሁና ዘመናቸው የፍቅርና የበረከት ዘመን መሆኑን ካልመሰከራችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ አትችሉም፤ ወይም በአዲስ አበባ ከተማ የመኖሪያ ቤት ፈቃድ አይሰጣችሁም እያሉ ከሚሰብኩት ወንጌል ያነገቡ ፖለቲካኞች አንዱ አቡነ ቀውስጦስ ናቸው።

እዛኝ መስለው በመድረክ ላይ የአዞ እንባ የሚያፈሱት እኚህ የወያኔ መልእክተኛ ከዚህ በፊት በዲሲ ቅድስት ማርያም፣ በደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤልና በሌሎችም አካባቢዎች የሚገኙትን ገለልተኛ ነን የሚሉ አብያተ ክርስቲያናት ለአባ ጳውሎስ እጅ መንሻ አድርገው ለማቅረብና ተወዳጅነትን ለማትረፍ ያደረጉት ሙከራ የራሳቸውን የጵጵስና ክብር ከማስደፍርና ቤተ ክርስቲያናችንን ካማስነቀፍ አልፎ ያመጣው ለውጥ እንደሌለ እርሳቸውም ያውቁታል። በራዲዮ፣ በጋዜጣና በኢንተርኔት ብዙ ተዘልፈዋል፤ ብዙም ተጽፎባቸዋል። እርሳቸው ግን ዓላማቸው ስለሆነ ወገንን ከወገን የማናከሱን ተግባር ሥራዬ ብለው ቀጥለውበታል። ሰሞኑንም በአትላንት ቅዱስ ገብርኤል የሚገኙ ምዕመናን ተመሳሳይ ዕጣ ደርሷቸው የአባ ጳውሎስ መልእክተኛ የሆኑት አባ ቀውስጦስ በሚቀጥለው ሳምንት ወደዚያ ተጉዘው አንድነታቸውን የሚያፈራርስ የጥላቻና የዘር ፖለቲካ ሊሰብኩላቸው የተዘጋጁ መሆኑን ማወቅ ችለናል።

*የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን!*

*ዛሬ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንቱ ድምፅ ታፍኖ እናትና አባታቸውን እየተሳደቡ ያደጉ ጋጠወጥ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ቅዱሳን በሚል ስም ቤተ ክርስቲያንን እንዲያፈርሱ እያሰለጠኑ ከሚልኳቸው ውስን ሊቃነ ጳጳሳት አንዱ አባ ቀውስጦስ ናቸው። አባ ቀውስጦስና መሰሎቻቸው ማኅበረ ቅዱሳንን ከፊት አሰልፈው በየቤተ ክርስቲያኑ ሁከት የሚፈጥሩት የራሳቸው ድብቅ ዓላማ ስለአላቸውና ከሚፈልጉት ግብ እስከሚደርሱ አብሮ መሥራት ግድ ስለሆነባቸው ነው እንጅ የአባ ጳውሎስ ውግዘት አሳሪ ነው፤ አሠራራቸውም ትክክለኛና ፍትሐዊ ነው፤ ብለው ስለሚያምኑ ወይም ከእርሳቸው ጋር ስለሚስማሙ አይደለም። ስለዚህም ነው ቅዱሳኑ አባ ቀውስጦስን ደጋግመው የሚያሸሞነሙኗቸው።*

*ፓትርያርክ የመሆን ጽኑ ምኞታቸውን በጋለ ስሜትና በአለባበስ መሽቀርቀር የሚገለጹት እኒህ ሊቀ ጳጳስ ከወራት በፊት ዲሲ ቅድስት ማርያም ሲደርሱ እንደ አባ ተክለ ሃይማኖት ጻድቅ ናቸው ብለው ገድላቸውን ሊጽፉ የተነሱ ተከታዮቻቸው እንደነበሩ ውሬው ብቅ ማለቱ አልቀረም። በጣም ይገርማል!! ደግሞ በዚህ ዘመን ቅድስና (ጻድቅነት) በሥራ መሆኑ ቀርቶ በአገር ልጅነት ሆነ እንዴ! ደግሞስ ወንድሞቹን የሚከስና መዕመናንን የሚያበጣበጥ ሰው እንዴት ደግ ሊሆን ይችላል?። ዱሮማ ሳጥናኤልም እኮ መልአክ ነበር። ክብርና ሥልጣን ሲፈልግ ነው ከማዕርጉ የተዋረደው። ሆኖም የእርሱ ውድቀት ለሰማይ ሠራዊት እፎይታን ፈጥሮላቸዋል፤ "ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፥ ደስ ይበላችሁ…የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና" (ራዕ 12፥10) ተብሎ እንደተጻፈ። መቸም እግዚአብሔር የቀባውን የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደእነ አባ ቀውስጦስ ደባ ሠርቶ ወይም በአፈሙዝ አስገድዶ ከመንበሩ ቢያወርዱት የተመኙት ሁሉ ያንን ሥልጣን ያገኙታል ማለት አይደለም። ዕድሜ ልካቸውን በሥልጣን ጥም አብደው ሲያበጣብጡ ይኖራሉ እንጅ። ሹመቱ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ካልሆነ በጉልበት ቢቀሙትም ያ ያገልግሎት ዘመን የበረከት ሳይሆን የመከራና የሁከት ዘመን እንደሚሆን በታሪክ ተረጋግጧል። የእኛም ቤተ ክርስቲያን የተባለው ነገር የደረሰባት ስለሆነ ይህን ለሌላው ትመሰክራለች።*

*ዛሬ የኢትዮጵያ ኦርዶቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጥብቃ የምትፈልገው አባት እንደ ሳጥናኤል ወንድሞቹን የሚከስ የጎሳ ፖለቲከኛ ሳይሆን እንደ ክርስቶስ ለመንጋው አንድነት ሲል ራሱን ቤዛ አድርጎ የሚሰጥ ታማኝ እረኛ ነው። ዛሬ ኢትዮጵያውያን የኦርቶዶክስ ምዕመናን አጥብቀው የሚፈልጉት እኔን ተከተሉ ሌላውን ጥሉ እያለ የአዞ እንባ የሚያፈስባቸው ሳይሆን ርሃብ የወጋው ጎናቸው፣ የፖለቲካኞች በትር የሰበረው አጥንታቸው እስከሚጠግን ድረስ በአንድ እግሩ ቆሞ የሚጸልይላቸው አባት ነው። እንግዲህ ይቅርባይነትን ከማን እንማራለን? ወይስ እነ አባ ቀውስጦስ ከማይፈልጉት ክፍለ ሀገር የተገኘ የቤተ ክርስቲያን አባት ለእርሱ ሲል ድምጻቸውን ከማይሰማበት፣ ዓይናቸውን ከማያይበት ዓለም መሰወር አለበት?።*

*ቸሩ አምላክ ለመንጋው የሚራራ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ እረኛን*
*እስከሚሰጠን ድረስ እንጸልይ።*